# ምሁር ሲሉ ጥሬ፣ ትግል ሲሉ ወሬ

## ወይም

## ከጅብ ጎፈሬ የአንበሳ መላጣ

ከተነሳሁባቸው ዋና ዋና መሰረተ ሀሳቦች ጋር በአላጢስም በረሀ ቢሆን አቋርጠው ሊገናኙ ይችላሉ የምላቸውን ሁለት ሀቅ ሆነው ጨዋታ መሰል "ታሪኮችን" ላቅርብ::

በመጀመሪያ ደረጃ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለን ጂዮግራፊ ስንማር አንድ ተንኮለኛ ተማሪ የሚያስተምሩትን በሚገባ የማያውቁትን አስተማሪያችንን እጁን አውጥቶ "የኔታ፣እርስዎ ወንዝ ሁሌም ወደታች ነው የሚፈሰው ሲሉን ይህ  የተለጠፈው የአፍሪካ ካርታ ላይ ስናይ ግን አባይ ከኢትዮጵያ ተነስቶ ወደላይ ወደ ግብፅ ነው የሚፈሰው" በሚል አፋጠጣቸው:: አስተማሪያ ችንም ምንም ቢሆን ከእኛ የተሻሉ ብልጥ ነበሩና ሲመልሱለት " ምን መሰለህ፣ ወደ  ላይም ቢፈስ እኮ በዘዴ አድርጎ በሽለቆ ነው" ሲሉ ሁላችንም ገባን ገባን ብለን አባይን በአንጎላችን ወደ ላይ አፍስሰን ተውናቸው:: ሁለተኛው ደግሞ በቅርቡ የሆነ ነው:: የዘመኑ የወያኔ የጎጥ በሽታ የተጠናወተው አንድ ፖለቲከኛ ነኝ ባይ ግለሰብ ከፎገራ የመጡን አንድ ካህን ሊያግባባ ፈልጎ "አባ እኔም እኮ የተወለድኩት ከፎገራ ነው"ሲላቸው "ፎገራ የት ቦታ ልጄ ? " ብለው ቢጠይቁት ይህ የወሊሶ ጮሌ "መተማ" ብሎ መለሰላቸው ተብሏል::

ሳያወቁ አወቅኩ ማለት:: ባልሆነ መንገድም ሊጓዙ ተነስቶ የምትሃት ዘዴና ሸለቆን ፍለጋ መግባት :: በጎጥ ፖለቲካ ዘቅጦ ገብቶ ሊያወናብዱ ሲሉ መጋለጥ::ከሁሉም በላይ ግን ውርደትን መልመድ መላመድ ተበራክቶ የፖለቲካውን መድረክ ዕርያ የሚገላበጥበት ጭቃ ሊያስመስለው ትንሽ ቀርቶታል:: ጎበዝ ተዋረድን እኮ፣መጫወቻ ሆንን እኮ፣ ብሎ ጮክም ብሎ ሆነ በለሆሳስ የሚናገረውን ደግሞ ቅፅል ከምሮ መቀጥቀጡ የሚቀናቸው በዝተዋል:: ይህም ተለመደና፣ ወንዝን በዘዴ ወደላይ የሚያፈሱ በረከቱና እስከ ፐ ተምሮ ዳግም በ " ሀ " ለመጀመር መገደድ ወይም መምረጡ አይቀሬ እየሆነ "እውነተኛ ቃላት ቆንጆ አይደሉም፣ቆንጆ ቃላት ደግሞ ሀቅ አይደሉም " የተባለውን ትምህርታዊነት ስተን ነጋ ጠባ መርገምን በፀጋነት እያቀፍን፣ትግልን በወሬ ደረጃ ገድበው ባቆሙ ተደናግረን፣ ሀ ያላለው ድጓ ያመ ድጓን የጨረሰ፣ መፅሀፉን ሁሉ የቀራ እየመሰለ ን፣ የዞረበትን ሊቅ ፣ ግራ የገባውን መንገድ መሪ ነው ብለን በማመን በተደጋጋሚ ከማጡ መስመ ጡ ዕጣችን ሆኗል:: ዓይን አውጣዎቹም ውሀ ወደ ላይ ይፈሳል፣ወያኔ ከተመክሮው ተምሮ ወደ በጎ ተቀይሯል፣ በወያኔ ፓርላማ ተብዬ የቧልት አዳራሽ ዴሞክራሲ ትወለዳለች፣ የተዘጋችው የዴሞክራሲ በር በሰላማዊ ትግልና ምለላ ትከፈታለች ፣ ከዚያም እውነት እውነት እላችኋለሁ በርገግ የሚለው በር የቃሊቲ እስር ቤት አይሆንም  እያሉ ሳያፍሩ ሊነግሩንና ሊያሳስቡን ሲነሱ ጆሮ አንሰጥም አላልናቸውም:: "ለገንዘብ ብሎ አምላክን አገለግላለሁ የሚል ሰው ብዙ ቢከፈለው ለሰይጣንም ያድራል" ነውና የቅደም ሆዴ ፖለቲካ አባወራዎች ለትግል የተነሱትን እያደናቀፉና

ክፍፍልን እያራገቡ በስልጣን ላለው ጭራቅ ሲሰግዱ ይህን ሆድና ፍርሀትን የማምለክ ሐጢያታቸ ውን ባማሩ ቃላትና ሰላም ፈላጊነት፤አልፎም ስልጡንና ብልህነት በሚል ሽፍነው ይውገረገራሉ፡፡

ታዲያ ይህ ሁሉ ህይወታቸውን የሰጡ ጀግኖች የፃፉትን ያስታውሰናል፡፡

አረመኔው የወያኔ ጥርቅም በግፍ ከገደላቸው የኢትዮጵያ ልጆች አንዱ የሆነው ጓድ ደረጀ "ትንሽ ግጥም ለአፍ የምትጥም" በሚል የሚከተለውን ፅፎ ነበር፡፡

" ሆነ አልሆነ ብሎ ይጨነቃል ዓለም
ከትግል የበለጠ ከቶ አንዳች የለም፡፡
መቻል ብሎ ነገር አንገት መድፋት ጣጣ
ለኛስ አይበጀንም ትግላችን ቀን ይውጣ፡፡
መተኮስ እንጂ ነው መግደል ገዳይን
አላስኖር አላስቀምጥ ያለ ሰው በላን፡፡"

ዛሬ ደግሞ ሊገድል የሚመጣን ለማቀፍና ለመሳም አሊያም ስስ ብልትን ለመጠቆም ወይም ገልጦ ለመስጠት መተባባር ይገባል የሚሉ ፕሮፌሰሮች በበዙበት ወቅት ይህ ሰው በላን በተመለከ ተ ሊኖረን የሚገባውን አቅዋም ግልፅ ያደረገ ማሳሰቢያ ወቅታዊ ነው፡፡ ሰብዕናቸውን ሽጠው ፍርሀታቸውን የተከተሉትን በተመለከተ ደግሞ የሕዝብ ጠላቶችን ሲዋጋ የተሰዋው ጂጋር " ይብላኝ ለእናንተ " በሚል በፃፈው ግጥሙ የሚከተለውን አስፍሮ ነበር፤
" ይብላን ለእናንት ለነትፋት ላሹ
ለፋሺስት መንጋ አጎንባሹ
ለነተቀልባሹ
ለመንታ ምላሱ
ለርግድግድ ወራዳ..አዳሪ ለከርሱ
ይይዝ ሚጨብጠው የሆነውን ላጣ
ሰው በላ ቅንዝንዝ አረመኔ መንግስት የሕዝቦች ባላንጣ፡፡
ወኔያችሁ ተሰልቦ እጅግ ዝቅ ብላችሁ እጅ ለምትልሱ
ይብላን ለእናንተ የድል አድራጊነት እምነታችሁ ከስቶ
ግለታችሁ በርዶ ወኔያችሁም ሽንቶ
ክንዳችሁ ርዶ ቆራጥነታችሁ ድፍረት ግፍጫችሁ ከመቅፅበት ጠፍቶ
ይብላን ሕዝብ ለከዱ
መተማመን ተስኗቸው ተሰቅጥጠው ለራዱ
ይብላኝልኝ ለከሀዲ
ተልከስክሰው ጭራቆችን ላመለኩ፡፡"

ዛሬ ሕዝብና ሀገርን ክደው ወያኔ የተባለ ጭራቅን ለሚያመልኩ፤ ለወያኔ ልንሰግድ ዕድል አጣን፤ “ወርቃማ” የክህደት ወቅት አመለጠን ብለው ሙሾ ለሚያሰሙ ይብላኝ ለእናንት መባሉ ሲያንስ ነው፡፡ ሌላ ገጣሚ ደግሞ “ሳሙና የሚሆን ስንት ዕፅ ተቀምጦ/ምነው ቅይጥ ተባይ በላነ መጥምጦ ያለውንም ማስታወስ ወቅታዊ ነው፡፡ እበት ትል እንዲወልድ ዘመኑ ጅል ወልዶ/ወዳጅ ነው ተባለ ጠላት ከፊት ቆሞ/ የተባለውም ቢጠቀስ ቦታው ነው፡፡ የፀጋዬ ደብተራውማ

“ ኪል ኪል ሲል የተስፋ ቃጭል
ጭል ጭል ጭል የብርሀን ፀዳል
ተግ ተግ የሰማዕታት አክሊል
ወገግ ፍኖተ ገድል ፍኖተ ድል” የሚለው ለእንፉቅቅ ሊቆች የሚጥም ሊሆን አይጠበቅም፡፡

ከሞት የከፋው መርሳት ነው የተባለውን ከተቀበልን ደግሞ ከሶሰት ዓመት በፊት በግፍ የተገደሉ ትን ሁሉ ከመቅፅበት ረስተን ዛሬ ገዳዮቻቸውን በብልህነት አወድሰን መሰረቱ ለላላ ጣያት ስገዱን ብንሰብክ ሀገርም፤ሕዝብም ታሪክም የሚታዘበን መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ የዚህ ሰበካ ጳጳሱ ደግሞ ከአፄው ዘመን ጀምሮ ሚናው ትጥቅ ማስፈታት ከሆነ ለዚህ ለጠነዛ ቅስቀሳ--ራሱን አዋቂ ፕሮፌሰር ወይም ዶክተር አለ አላለ-- አማኝ ጆሮ መስጠቱ ራሳችንን የሚያስገምተን መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ስድ የለመደ ፤የኋልዮሽ ጉዞ የተጠናወተው፤ ውርደትን ክብር ያለ ፤ራሱን ና ፍርሀቱን ማቾነፍ ያቃተው፤ በላያ ተራራ ወይ ደጀን ላይ ሳይሆን በዋሺንግተን “ተራራ” ወጥቼ ሀቅን እፈልጋለሁ ባዩ፤ ክህደትን ስልጡን ፖለቲካና ብልህነት ብሎ አቃፊው፤ ለወያኔ መስ ገዱና መዋረዱን ወርቃማ ዕድል ባዩ፤ በአጭሩ ራሱንና ሀገርን አዋራጁ አርአያ ሳይሆን ማፈሪያ መሆኑን ሁሉ ሊያወቅበት ይገባል፡፡ ይህን ሀቅ መረዳት ሲያቅታቸው እነሆ ብለን በግልፅ ቃልና መልዕክት ልናስረዳቸው ስንነሳ ደግሞ ዘለፉን፤ ተተናኮሉን፤ በድንቁርናችን ጣልቃ ገቡ ወዘተ እያሉ መልሰው እኛኑ ማውገዙን መርጠዋል፡፡ ሀገርና ሕዝብ ተደፍረው ሳለ፤ የሕዝብና የሀገርን ጥቅም አሳልፈው እየሰጡ ተዉ ስንላቸው ተደፈርንን ይጮሁብናል፡፡ አዙሪቱ ለእርምት ሳይሆን ለባሰ ዝቅጠትና ውዥንብር በሩን ከፍቶ የዚህ መድረክ አለቃ ወያኔ የሚወራጭበትና የሚፎክርበ ት ሰፊ ዕድል አግኝቷል፡

የችግሮችን መንስዔዎች፤ ይዘትና አንደምታም ስናጤን በግድ የምርመራውን መብራት በራሳችን ላይ ማነጣጠሩ አስፈላጊ መሆኑ የሚካድ ሊሆን አይችልም፡፡ ከሀገር ወዳድነት ጀምሮ (ለአንዳን ዶችማ ሀገር ከሚለው ተነስቶ) እስከ የትግል ትርጉምና ይዘት ድረስ እያንዳንዱ እርምጃ በእንቁላ ል ላይ ሩጫ እንዳይሆን ግልፅነትና ከስህተት መራቅ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የወያኔ አገዛዝ አረመኔነ ት እሰጥ አገባን ጠያቂ አይደለምና ለዚህ አረመኔ ራሳችንን ደግመን ደጋግመን ሰለባ ካደረግን ራሳችን ተጠያቂ መሆናችንን ልንክድ አንችልም፡፡ ከ 1983 ዓ.ም. በፊት ስለ ወያኔ ፀረ ሕዝብነት ብዙ ሲቀሰቀስ አልሰማ ያሉ ጆሮዎች ጥቂቶች አልነበሩም፡፡ ሰው በላዎቹን ልጆቼ ያሉትን አደና ጋሪዎችንም አክብረው ያዳመጡና አልፎም መሪዎቻችን ሊሉ የተነሱም ብዙ ነበሩ፡፡ በግርግር

ወያኔ ስልጣንም ሀገርም ሰረቀ ብንል ማጋነን አይሆንም። በ1997ም ከምርጫው በኋላ የተከተለው ፍጅት የወያኔ ወንጀል መሆኑን የሚክዱ ያው ለደርጉ ቀይ ሽብር ወንጀል ሟቾቹን በሃላፊነት የሚከሱ ንስሐ የከበዳቸው ነፍሰ ገዳዮች ወይም የፋሺስት አማካሪዎች ብቻ ናቸው። ነገር ግን የሕዝብ ድል ሲነጠቅ የነጣቂው ወንጀል እንዳለ ሆኖ የሰለባዎቹም ማለትም የእኛም ሃላፊነት ደግሞ ተደብስብሶ ካለፈ ስህተትን ለማረም የሚያግድ ይሆናል። በተለይም በአሁኑ ጊዜ በኬንያ ና በዚምባብዌ የተከሰተውን ስናይና የሁለቱን ሀገር ተቃዋሚዎች (የምዕራባውያንንም ሚና ) አቅዋምና ትግል ስንታዘብ በእኛ በኩል የነበረውን ድክመት እንረዳለን። ወያኔ ከስህተቱ ተምሯል የሚሉ ክፍሎች ያኔም ተጠራቅመው የሕዝቡን ትግል ያልፈሰፈሱና ለአደጋ ያጋለጡ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ "ወገኛ በባዳ ምድር ልሁን ይላል ሰርገኛ" እንደተባለው ማንነታቸው የማይታ ወቅ ይመስል የትጥቅ ትግል ድንገተኛ አባወራ ነን ብለው መጮኽ መጀመራቸው ሌላ የነገን ሁኔታ ሊያደፈርስ የቃጣ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ትግላችን ለድል ደርሶ የተደናቀፈው በጠላት ኃይለኛነትና ብልህነት ሳይሆን መሪዎች ብለን በሰየምናቸው ወይም አመኔታ በሰጠናቸው በተፈፀ ሙ በርካታ ስህተቶች የተነሳ መሆኑ ዛሬ ግልፅ ነው። ለዚህም ተጠያቂ ራሳችን ነን። ለምን ሲባል አንድም የሀገር ወዳድነትን ትርጉም ዝቅ አድርገን በማቅረብ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ማን ሀገር ወዳድ ማን የሕዝብ መሪ ለሚለውም መልሳችን ራሱን አውቆ ፍርሀቱን ማሸነፍ ያልቻለውንም ጀግና የሚያደርግና፣ ለሆዱና ይህንን ጥልቅ ጉድጓድ ይሞልሉኛል ለሚላቸው ባዕዳን ያደረውን መሪያችን በማለታችን ነው። በተወሰነ ደረጃ ሀገርን ሲወዱ ልክ ልጅን ሲወዱ ከእነምኑ በተባለው ዓይነት ሊሆን ቢችልም በሀገራችን ያሉ ጎጂ ባህሎችና መጥፎ ልምዶች አቅፈን ልናስተናገድ መጠበቅ የለበትም። በ 1973 በሀገራችን ረሀብ ሲገባና ለተራበው እርዳታ ለማሰባሰብ ጥረት ሲደረግ ረሀብ መከሰቱ የስርዓቱ ውድቀትና ድክመት መሆኑ ቀርቶ የሕዝባችን ጥፋት ይመስል ያፈሩና የተደበቁ ወይም ረሀቡ የለም ያሉ ነበሩ። በሀገራችን ጎጂ ባህሎች አሉ--ሀገራችን የምንወ ዳት እነዚህን ልናስወግድ ስንነሳ እንጂ የእኛ ብለን ስንይዛቸው ወይም ስንደብቅ አይደለም። በርካታ ኢትዮጵያውያን ወራሪ ጠላቶችን በጀግንነት ቢዋጉም በዚያው ልክ ባንዳውና ከሀዲው መርመስመሱና ለወራሪ ቪቫ ያሉ እንደነበሩ ማወቅና ማመንም ፀጋ ነው። በዘመነ ደርግ ብዙ ሚሊዮን ሕዘብ ተርቦ አልቋል። በወያኔ ደግሞ ብዙ ሚሊዮን ዛሬም ለረሀብ ተዳርጓል። ይህ የሀገ ራችን እውነታ ነው--ተጠያቂው ህዝብና ሀገር ሳይሆኑ አገዛዙ ነው። በቀይ ሽብር ጊዜ ታጋይ ክፍሉን ያጋለጡ ወይም ርዳታ ያልሰጡ ብዙ ናቸው--ሀፍረታችን ነው። ስለዚህ የወያኔን ገበናና ግፍ መደበቅ ሳይሆን ማጋለጡ ይገባል። በሀገራችንብዙ ግፍ ተፈፅሟል፣አረመኔነት ተከስቷል። ይህ የወንጀለኞቹ ማፈሪያ እንጂ የሀገርና የሕዝብ ሀፍረት አይደለም። ስለዚህም ሀገርን በመውደ ድ ሽፋን ወይ ማጠየቂያ ጎጂ ባህሎችን፣ የግፍ ድርጊቶችን፣የአገዛዞችን ብልግናና ድክመታችንን መሸፋፈኑ ትክክል አይደለም።

በዚሁ ልክ ደግሞ የታሪካችን ቆሻሻ ገፅታ ወይም መርገም የሆነውን እንዳልነበር ቆጥረን መማር
የሚገባንን ትምህርት መቅሰሙ ተስኖን ዳግም በስህተት ብንዘፈቅ ጥፋቱ የራሳችን ነው፡፡ አፄ
ኃይለ ስላሴ በአርበኛና ባንዳ መሀል ያለውን ትልቅ ልዩነት በጉልበት ሰርዘው በተለይም የባንዳን
መንጋ ሲሾሙ ሲሸልሙ ( እነ በላይ ዘለቀን ስቅለውና ሌሎችን አግልለው) ያፀደቁት መርህ
መዘዙ ቀጥሎ የሞተልሽ ሳይሆን የገደለሽ በላ የሀገራችን የማያባራ ምፀት ሆኖብን እስከዛሬ ዘልቋ
ል፡፡ ሀገሪቷን የጎዳና የከዳው ዋጋውን ማግኘት ሲገባው/ማለትም መቀጣት/ በተገላቢጦሽ ቦታ
እየተሰጠው ለሀገር ህይወቱን ሰጥቶ መከራ ያየው ደግሞ እየተክቸለቸለና እየተሰደበ ቆይቷል፡፡
የብልህ ምሳሌ የሆኑት ለአፄውም ለደርግም ያገለገሉትና ሁለቱንም አገዛዞች የመከሩትና ሎሌ
ሆነው የረዱት ሆነው ታጋዮቹ ግን መረገማቸው የታየ ነው፡፡ ጀግናና አርበኛ ትርጉሙ ጠፍቷል፡፡
ለነገሩ ወደ አሜሪካም ዓይናችን ከሄደ የሰው ሀገር ሰው በአይሮፕላን ድብድቦ፤አይሮፕላኑ ሲመታ
ወርዶ የተያዘና የታሰረ ግለሰብ ጀግና ተብሎ ሲደነቅና ለፕሬዚዳንትነትም ሲታጭ
እያየን ነው፡፡ የአፍሪካ ቅኝ ገዢዎች የየሀገራቸው ታላቅ መሪዎች ተብለው ተደናቂ ናቸው፡፡
ያን በዚያ ለእነሱ እንተወውና በሀገራችን ምንቸቶች ጋን መሆናቸው ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ
ይችን ያልታደለች ሀገር ያደሟት እየተወደሱ የሞቱላት እየተወገዙና እየተከሰሱ እስካዛሬ ደርሰና
ል፡፡ በወያኔ የተተካው  ፋሺስታዊ አገዛዝ ደግሞ ሀቀኝነትን ቀብሮ፤ፍርሀትን አንግሶ፤ ለምን
ያሉትን ገድሎ፤ ሕዝብ ይቅደም ያሉትን ጨፍጭፎ፤ ለዓላማ መቆምን  ሀገሬ ማለትን ከሞት
አቆራኝቶ፤ ማቀርቀር-- መሳንበስ-- መሰንበት-- መበርከት-- ፖለቲካና ኮረንቲን በሩቁን አስፍኖ
 በመቆየቱ ገበያው ሳይደራ እናቱን የሚያስማማው የወያኔ መንጋ አልጋ በአልጋ ሁኔታ አግኝቶ
እነሆ በላያችን ላይ ህድሞውን ሰራብን፡፡ ያን ሁሉ ውድ ህይወት የቀጠፈውን አረመኔ መንጌ መን
ጌ እያሉ በግልባጩ የተጨፈጨፈውን ወገን ደግሞ በነጭ ሽብር ካልተከሰሰ ብለው ነጋ ጠባ ኡ
ኡ የሚሉና ዛሬ ደግሞ ለወያኔ ስላደሩ በወያኔ ተይዘው ደብዛቸው የጠፋውን የካዱና አናውቅም
ያሉ የሕዝብ መሪ ተብለው ሲደነቁ አልሰማንምን? ይህ የተበላሸ ሁኔታ ይበልጥ እየጨቀየ ሄዶ
ሕዝብም መሪ ማን የሚለውን በጥንቃቄ መገንዘብና መምረጥ አቅቶት በራሱ ላይ ሽክሞቹን
ማስቀመጥ የግድ ሆነበት፡፡ ሞኝ ሰው ወንድ ልጁን ተሸክሞ ሴት ልጁን በጭቃ ሲጎትት የታዘቡ
አዛውንት ነብርን በጫንቃ ወርቅን በጭቃ ያሉትን ያስታውስናል፡፡ በመሰረቱ መሪ ሊሆን የሚገባ
ው በአርአያነት፤በጀግንነት ያንን ቦታ ሕዝብ በውዴታ የሚሰጠው ነው፡፡ ራሱን ኮፍሶና አዋቂ
ብሎ መሪ በሉኝ ያለውን ወደ ሌላ ቦታ መወርወሩ ተገቢ ነው፡፡ መሪ ስንል መሪ ሲሉ ብለን ከተነ
ሳን ፈሪ ተለይ የተባለበትን ዘመን ፤ያን ጎራዴ መዘው ታንክን የተጋፈጡ ጀግኖች የሰፈኑበትን
ጊዜ እንኳን ብንተው  በቅርባችን ሞት ለፋሺሲት ብለው ፤የትግሉ ነው ህይወቴ ብለው የተሰዉት
ን መጥቀስ እንችላለን፡፡ ከሁሉም በፊት ሞት አይፈሬ ሆነው በመስዋዕትነት አርአያ የሆኑት፡፡ ዛሬ
 በአርአያነትና በመስዋዕትነት፤በጀግንነትና መከራ ቻይነት መሪ የሚሆኑ ሳይሆኑ ዶክተር ነን
መሪ አርጉን፤ ክቡር በሉን፤ሀብታምም ነን በነገራችን ላይ ወዘተ የሚሉና ገና ባሩድ ሳይሸተው፤
ሞት ሳይመጣበት፤ ወዳጅ እስረኛ  በሚል ፈሊጥ ተቀማጥሎ እያለ ወኔው/ያውም ከነበረ!/ የከዳው
ን አስመሳይ፤ኳ ቢል ሿ ክንብሉን  መሪ ብሎ ማሞገሱ ሰፍኗል፡፡ ይባስ ብሎ ገናያልተፈተነውን

ፅኑ፤ ስለ ትግል ያለው ግንዛቤ ገለባውን አዋቂ፤ ታሪኩ የሸሸት፤ የክህደት፤ የበታኝና አንጃነት የሆነውን የሕዝብ መሪ ብሎ ማቀፉ፤ ድፍን ቅሉን ምሁር፤ስለ ትግል የሚያወራውን ታጋይ አድር ጎ በላይ ላይ ማስቀመጡም ቀጥሏል። በመሆኑም ዴሞክራሲያዊ ነን እያሉ ጫማ የሚያስሙ፤ ከፖለቲካ ችሎታና ዕወቅት ጋር የማይገናኘውን ቅፅላቸውን ለጥፈው ስገዱልን የሚሉ፤ በሀመርና ሊሞዚን መኪና ካልሄድን ተናቅን የሚሉ ግብዞችን መሪ  በሚል ሆ  ሆ ብሎ ማጨብጨቡ ንቃት ተብሏል። ይህ ስህተት ነው ብንል ምን አጠፋን? በተለይም ለስልጣን በቅተው እስኪለጉሙን ድረስ!

ከዚህ ተያይዞ ወይም የዚህ መሰረት ሆኖ የመጣው ግን አሳፋሪ ምርጥነት ወይም አንዳንዶች የሚሉት ልሂቅነት ነው። የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የራሱ የሆነ ዕውቀትና ብልህነት ያለው መሆኑ ተክዶ በሕዝብ ላብ ተማርን ያሉ በዚሁ ያገኙትን ወረቀት በማውለብለብ በሕዝብ ላይ የበላይነት ና የንቀት አቅዋምን ሲያንፀባርቁ ማየት ተገደናል። የተማረ ያልተማረ፤ ዲግሪ ያለው የሌለው የሚለው መመዘኛ፤ ጀግና ወይስ ፈሪ፤ ሕዝባዊ ወይስ ግለኛ፤ መርህ ያለው ወይስ አድርባይ፤ ሀገር ወዳድ ወይስ ሆድ አምላኩ ፤ባንዳ ወይስ አርበኛ የሚለውን ሊተካ ሲፍጨረጨር እያየንም ነው። ዛሬ ጀግና መሪ በማለት ፈንታ ዶክተር ወይም ኢንጂኔር ወይም ፕሮፌሰር ማለቱ ቀድሟል። ዶክተር ሀኪም ነው፤ ኢንጂነር ህንፃ መንገድ ገንቢ ነው፤ የከብት ሀኪም የከብት ሀኪም ነው፤ ወዘተ --ታዲያ ይህን ከፖለቲካ ዕወቅት ወይስ ከፖለቲካ ንቃትና ቆራጥነት፤ ከሀገር ወዳድነት ጋር ምን አገናኘው? አቶስ ፤ወይዘሪት ወይዘሮስ ምን አጠፉ? ምሁር የሀገር ቅርስ ነው--ለሀገርና ለሕዝብ ከቆመ ። ምሁር የሀገር ዕዳና መከራ ነው-- የጨቋኝ አገዛዝ መሳሪያ ከሆነ። በናዚዋ ጀርመን ዶክተር ጎብልስ የሂትለር ቀኝ እጅ ነበር። የመንግስቱ ኃይለማርያም ቀኝ እጅ ምሁሮችስ ተረሱ? ዛሬስ ከወያኔ ጋር የተሰለፉ? ሕዝባዊ ምሁር፤ፀረ ሕዝብ ወይም ሆዳም ምሁር የምንለው ለዚህ ነው። የሕዝብና የድርጅት መሪዎች የሚከበሩት በሕዝብ ላይ ተንፈራጠውና ተኩራርተው ምሁር ልሂቅ ነን ብለው ስለተገበዙ መሆን የለበትም። ክቡር እገሌ በሉኝ ስላሉም ሊሆን አይችልም። መሪዎች የሚከበሩት በረሀብ ሕዝብ ሲያልቅ፤ እነሱን ተከትለው የተሰዉ ጀግኖች ቤተሰቦች ረጂ አጥተው መከራ እያዩ ባለበት ብዙ ሺ ዶላር ወይም ብር ተከፍሎ በእንድ ልቅ መኪናዎች መኳዛቸውና በውድ ሆቴሎች በመቀመጣቸው አይደለም። የመሪዎች መለያ ሕዝባዊነት፤ ትሁትነት፤ ሞት አይፈሬነትና በተጨባጭ ትግል አርአያነት መሆን ነው። ያልቆሸሸ ታሪክም ያስፈልጋል። የፋሺስት ቡድን አማካሪ፤ የባዕድ ቅጥረኛ፤ እጁ በንፁህን ደም የተጨማለቀ ፤በክህደት፤ብተናና አንጃነት ድርጊት የተሰማራ፤ የሕዝብ ትግል መሪ ሊሆን ልትሆን አትችልም። ዛሬ በአንዳንድ ድርጅቶችና በነፃ አውጪ ነን ባይ ቡድኖች ተሰግስገው ያሉ ወንጀለኞች ቢያንስ ግንባር ቀደም ሚናን ሊጫወቱ ቦታ ሊሰጣቸው አይገባም። ለንስሃና ለይቅርታ ያለው ቦታ እንዳ ለ ሆኖ በደፈናው የትላንት ወንጀለኛ ተመሳስሎ የዛሬ አርበኛ የሚሆንበት መንገድ መዘጋት አለበ ት። ሕዝብም ለክብሩና ታሪኩ ብቁ የሆኑና የማያሳፍሩ መሪዎች መያዝ ሲገባው በራሱ ላይ በተቃዋሚ ሽፋን ሊነግሱበት የሚከጅሉትን መቀበል አይገባውም። የሕዝብ መሪዎች ደግሞ ሕዝብ የሚጠላውን መስለው የሚገኙ ሳይሆኑ ቀናና ዴሞክራሲያዊ ገፅታን የሚያሳዩ መሆን

አለባቸው፡፡ በቅርቡ ከቃሊቲ ምህረት ጠይቀውና ተለቀቅን ብለው የሞተላቸውን ሕዝብ ሳያመሰግኑ ወደ ባዕድ ሀገር ቀልጥፈው የተጓዙት ግለሰቦች በባዕድ አይሮፕላን ጣቢያ ስዩመ መለኮት ነኝ ይሉ እንደነበሩት አፄ ጫማ ሲያስሙ፤ በሊሞዚንና ሀመር ውድ መኪናዎች እንደ ሆሊውድ ተዋንያንና ሀብታሞች ሲጓዙና ከሚሊዮኑ ህዝባችን በተለየና በመጠቀ ገዋ ሲንሳፈፉ ያየ ግለሰብ እነሱናሕዝብ ለየቅል መሆናቸውን መረዳት የሚችልበት ሁኔታ ነበር፡፡ ጉድ በማለታቸው ከተወገዙት አንዱ ብሆንም ሳይውል ሳያድር ክብርት ወይዘሮ ነፃነት/ሌዲ ሊበርቲ/ ተብላ የነበረችውም ወደ መጣችበት ተመልሳ ወያኔያዊ ሰልፏን አሳምራ ላሞገሷት ሳይቀር ማፈሪያ ሆናለች፡፡ ግለሰቧንም ሆነ መሰሎቿን የማይተቹና የማይነኩ ናቸው ብለው አፋችንን ሊለጉሙ የተነሱ የነበሩ ቢሆንም የሕዝብ መሪ ነን ብለው እስከተሰየሙ ድረስ ማናቸውም ቢሆኑ ከሕዝብ ትችት በላይ አለመሆናቸውን ማስረዳታችን አልቀረም፡፡ ፖለቲካ፤ ስልጣንና የፖለቲካ መሪዎችን ከሰማይ ሰቅሎና ምርጥ ይዘት ሰጥቶ ሰፊውን ሕዝብ አሽማቆና ዝም አሰኝቶ መግዛትን ወይ ለመግዛት መከጀልን አሻፈረን አንቀበልም ብለን ከሸፈትንና ለዓመታት ከታገልን በኋላ ዛሬ " በመሄጃው ጨርቆስ" እንዲሉ ያውም በትግል ላልተፈተኑ የጣዖት ምስላቸውን ቀርፀን ልንጎነበስ መጠበቁ ድፍረት ነው እንላለን፡፡ ስለዚህም መሪ ሲሉ መሪ ስንል ብለን በግልፅ መተቸት መብታችን ብቻ ሳይሆን ግዴታችንም ነው፡፡ ይህን ያልተረዱ ወይም ተጋለጥን ብለው በቁጣ ሊወርዱብን የተነሱት ወይም ይናደፉሉ እያሉ ወይም ጣልቃ ገቡ እያሉ በመለፈፍ ፀጥ ሊያሰኙን ቢችሉ ኖሮ ደግሞ ከቶም እስካዘሬ ፅንተን ባልታገልን ነበር፡፡

ከባለጎፈሬ ጅብ መላጣ አንበሳ ይሻላል፡፡ ሀገርን በግማሽ ማዳን አይቻልም፡፡ በፖለቲካ ግማሽ ጎፈሬ ግማሽ መላጣ ቁንጥ ሳይሆን ጎጂ አድርባይነት ነው፡፡ለዚህም ነው በሀገር ጉዳይ ላይ የጅብ ጎፈሬን ትቶ በአንበሳ ድፍረት በሙሉ ልብ ለመታገል መነሳት የሚያስፈልገው፡፡ ያ ሁሉ ንፁህ ደም ፈሶና ስንቱ ሺ በማጎሪያዎች ዛሬም ስቃዩን እየተቀበለ ባለበት አረመኔዎቹ ተሻሽለዋል ብሎ መስበክና በሕዝብ ቁስል ላይ ማላገጥ መቸም ወንጀል ቢባል ሲያንስ ነው፡፡ ወያኔን መፋለም ሲገባ እንቀፈው ብሎ መጃጃሉ ሀገርን ያስጠቃል፡፡ በእርግጥም ይህ መጃጃል ከሞላ ከርስ የመጣ ሊሆን ይችላል-- ውሻ በበላበት ሲጮህ ስንሰማ የመጀመሪያችን አይደለምና፡፡ የቀዳዳ ፍራንክ ዋጋ ዜሮ ከሆነ ጊዜ ያለፈ ነውና በተለምዶ አነጋገር የመንደር አውደልዳይ የሚባለውን ሁሉ በጀግኖች መንደር መፈረጁ የሚጠቅም አይሆንም፡፡ ከዚህ አልፎ ደግሞ ሀገርና ሕዝብን የበደለው ሁሉ ለቅንጣትም ታህል አጥፍተን ነበርን ሳያሰማ ከሕዝብ ግራ መደባለቅ ብቸ ሳይሆን በመሪነትና ነፃ አውጪነት ለመደብ መነሳቱ ራሰንም ማዋረድ ሀገርንም መሳቂያ ማድረግ ይሆናል፡፡ በሰማዕት ደም፤ በታሰሩትና በተጋዙት መከራ፤ ደብዛቸው በጠፋው ሰቆቃ መቀለድ ይሆናል፡፡ሕዝብ የራሱን ንፁህና ሀገር ወዳድ መሪዎች ይዞ ቀርጦ መታገል ይገባዋል እንጂ እምባጮዎችን በዱላነት ሊገለገል መነሳት የለበትም፡፡ የታሪክ ሂደት ጭንቅ ወደሞላበት ወቅት ሲደርስ የብዙዎች ወኔ ማጠጡና ክህደት መበራከቱ ያለና የሚኖርም ነው፡፡ የሕዝብ ጎራ በአስመሳይ ታጋዮች፤በምርጥና አዋቂ ነን ባዮች፤ ጠላት ወዳጅ ሆኗል በሚሉ አደናጋሪዎች ሲሞላ የተጠንቀቅን እምቢልታ መንፋቱ

የግድ ነው:: ዛሬ በአንድ ሀገር በኢትዮጵያ ሁለት ዓለም አለ:: የወያኔና ጭፍሮቹ፤ የቅምጥሎቹና የደላቸው ኑሮ በአንድ በኩል:: በሌላ በኩል ደግሞ የሚተኛበትን አቧራ መስሎ ተርቦና ተጎሳቅሎ የሚኖረው ሚሊዮኑ አለ:: ሁለቱ ዓለም ጎን ጎን ሊሄድ የሚችል አይደለም:: ጨዋ ሕዝብ ፤ ስነ ስርዓት አክባሪ ሕዝብ ተብሎ በበሉና በጠገቡ የሚደለለው ና ከትግል እንዲርቅ የሚደረገው ሕዝብ ያለው ትዕግስት ማለቂያ የሌለው አይደለም::የተራብ ሕዝብ በጠገበ ጨቋኝ ላይ መነሳቱ የሚጠበቅና ፍትሀዊም ሀቅ ነው:: ይህ ቀን ነገ ሳይሆን ዛሬ ይሆን ዘንድ ሳይታክቱ መታገልና መጣር ያለባቸው ተቃወሚ ድርጅቶች ናቸው እንጂ በተጋለቢጦሹ በአብዮቱ ወይም ሕዝባዊ አመፅ እሳት ላይ እሳት አደጋ መከላከያ ሊሆኑ አይገባም:: የተራበውና የተበደለው በጠገቡትና ህሊናቸው ላይ ተኝተው በሕዝብ በሚቀልዱት ላይ መነሳት አለበት:: ጨዋ ሕዝብ ውርደትንና ጭቆናን ከምቀበልና ከምችል ታጋዬ ልሙት ልሰዋ የሚለው ነው:: ጨዋ ኢትዮጵያዊ በጨቋኙና ሀገሩን ባዋረደው ኃይል ላይ አምፆ የሚነሳውና የባንዳን መንጋ ሁሉ የሚፈረካክስ ብቻ ነው::